# ኧረ እንዴት ዝም እንበል !

ከዓሣዬ

ጥንት ኣባቶቻችን ፡ ዕራፊ ጨርቅ ለብሰው
በባዶ እግራቸው ፡ ጋራ ሸንተረሩን ፡ በረሃን ኣቋርጠው
ባለ መድፍ መትረየሥ ፡ ጣልያኑን ኣሣደው
በጦር በጎራዴ በጋሻ መክተው
የእናት ኢትዮጵያን ቃል ኪዳን ኣንግበው
በጀግንነት ወድቀው ፡ ውድ ሕይወትን ከፍለው
ኣሥረክበውን ነበር ፡ ነፃ ኣገር ኣውርሰው ።
ግና !
ኣሁን በኛ ግዜ ፡ በሃያኛው ዘመን
በጠባብ ዘረኛ ! በደላላ ምሁራን ኣገር ሥትበተን
ቁም ነገር ሣንሰራ እጅና እግር ኣጥፈን ፡
ገደል ኣፋፍ ቆማ ! ኣድኑኝ ሥትለን ኧረ እንዴት ዝም እንበል ?

እነ ሥም ኣይጠሩ ፡ እነ እንጨት ሸበቱ
የሕዝብን ድል ሰርቀው ፡ ለጠላት ማሥረከብ የተካኑበቱ
ደግሞም ግንቦት ሰባት ፡ የሻቢያው ቱልቱላ ፡ ሞገደኛ እሣቱ
የሣልቫጅ ምሁራኑ ዜሮ ደናቁርቱ ፡
በባዕድ ጌቶቻቸው ፡ የተደገሠውን ጨማ እየዋጡ
በደሥታ ሢያውካኩ ፡ ውሥኪ እየተራጩ
ከርሣችን ከሞላ ፡ ኪሣችን ካበጠ ፡ የኛ ዴሞክራሲ እቺ ናት እያሉ
ዕርመ በላዎቹ ፡ ሊሸጡን ሢያሥማሙን ፡ ዝም ብሎ ማየቱ ፡
እኮ እንዴት ይሆናል ? ዕልቂት ሣይመጣብን ኧረ መላ ምቱ ። !
ዝምታማ ለበግ ፡ ከቶ መች ተመቻት
ካራውን ሥትልሰው ፡ የሚምራት መሥሏት
መቼ ልቡ ኣዝኖ ፡ ሂጅ ብሎ ለቀቃት ?
ኣንገቷን ገዝግዞ ! ሥጋዋን መትሮ ፡ ጠብሶ እኮ ነው የበላት ። !
እና ኣሁንም ቢሆን ፡
እኛ ሣንመርጣቸው ፡ በባዕዳን ተመርጠው ፡ ሲደራደሩብን

በጎልውናችንና ፡ በዕጣ ፋንታችን ሲፈጣጠሙብን፡
ኣንገት ኣቀርቅረን ዝም ብለን ምናየው
ልክ እንደ በጊቷ ፡ እሥክንታረድ ነው ? !
ኧረ የጀግና ያለህ !
በዓይናችን እያየን ፡ በጆሮ እየሰማን
ታሪኳ ተፍቆ ፡ ኣገር ሥትበተን ፡ እኮ እንዴት ዝም እንበል ? ።

በሥልጣኑ ባልጎ ፡ ወገንን የሸጠው ፡ ይኼ ጉዱ ካሣ
በዶላሩ ሰክሮ ፡ በመርዝ እሥትንፋሱ ፡ ተውሣክ እያገሣ ፡
ፋሺሥቱ ከበደ ፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጥቃቱን ጨመረ
በግዳጅ ኣዝምቶ ፡ ብዙ ሺህ ሠራዊት እንዳላሥመተረ ፡
ዛሬም እንደገና ፡ ያንን የኣገር ገንጣይ ፡ ወዳጅ ነው እያለ
ሻዓብያው እሣያሥ ፡ ልክ እንደ ፋሺሥቱ ፡ ዝንብም ኣልገደለ
እንዳውም ለኢትዮጵያ ፡ ባለውለታዋና ኣዳኟዋ ነው ኣለ ። !

ዕርፍ በሉ እንግዲህ ! የሥብሰባው ግብዓት ሲፈተሽ ሚሥጥሩ !
**ሴራው በግልጽ ታይቷል ! ለኣገር ብተና ነው ኣትጠራጠሩ ። !**
ኧረ ያገር ያለህ ! ኧረ የጀግና ያለህ ! ኧረ የዓመጽ ያለህ !
እንዲህ ሴራው ሲጠፍ ፡ በከርሥ ኣደር ጠላት
ሰርግና መልሥ ሆኖ ፡ ተዝካሯን ሊበሏት
ከሃዲ ባንዳዎች ፡ ሽር ጉድ እያሉ ፡ ካራ ሲሥሉባት !
መተኪያ የሌላትን ፡ ኣንዷ ኣገራችንን ጨርሰን ሣናጣት
ከዜጎቿ በቀር ፡
ሤራውን ኣክሽፎ ፡ ኢትዮጵያን የሚያድን ሌላ ሥሌለላት
በዓናችን እያየን ፡ በጆሮ እየሰማን ፡ ኧረ ችላ ኣንበላት !
ከእንግዲህሥ ወዲያ !
በኣንድነቱ ሃይል ! በኢሕኣፓ ዙሪያ እንደራጅና እየታገልንላት
ይልቅሥ ከሞቷ ላንዴና ለሁሌም በቶሎ እናድናት !
ኣዎ ! እሥቲ እባካችሁ ! ዜጋ ተሠባሥበን ከሞቷ እናድናት ። !

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል !

November 11/2015 G C.